የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/1123/14
ቀን/Date ጥር 25 2014

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/4088 ቀን 23/05/2014 በተጻፈ ደብዳቤ ቀደም ሲል ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቁጥር ማኢ.30/47/57 ቀን 24/09/2013 በተጻፈ ደብዳቤ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሲፈቀድ ተሽከርካሪዎቹ ያገለገሉ ከሆኑ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ መሠረት ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው መሆኑ መገለጹን በማስታወስ በታሪፍ መጽሐፉ ትራክተር በአንቀጽ 87.01፣ የቆሻሻ ማስወገጃ ማሽነሪዎች እና ዴሊቨሪ ቫን በአንቀጽ 87.04 እና 87.05 የሚመደቡ እና አምቡላንስ ይህ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ደብዳቤ እስከወጣበት ቀን ድረስ የተጫኑ ሆነው ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ለመጨረሻ ጊዜ ፀንተው ስራ ላይ ባሉ ህጎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ ሲፈቀድ የአገልግሎት ዘመን መሠረት ተደርጎ ከተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ጭምር ነጻ እንዲሆኑ የተፈቀደ መሆኑን ገልጿል።

በመሆኑም የገንዘብ ሚኒስቴር ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት በታሪፍ መጽሐፉ አንቀጽ 87.01 የሚመደብ ትራክተር፣ በታሪፍ መጽሐፉ አንቀጽ 87.04 እና 87.05 የሚመደቡ የቆሻሻ ማስወገጃ ማሽነሪዎች እና ዴሊቨሪ ቫን እንዲሁም አምቡላንስ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ደብዳቤ እስከወጣበት ቀን (23/05/2014) ድረስ የተጫኑ ሆነው ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ለመጨረሻ ጊዜ ፀንተው ስራ ላይ ባሉ ህጎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ ሲፈቀድ የአገልግሎት ዘመን መሠረት ተደርጎ ከተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ጭምር ነጻ ሆነው እንዲስተናገዱ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፈቀደበትን 01 ገጽ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቀበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፤</u>
- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለታሪፍ ምደባና ሥሪት ሀገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>
- ለፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት
- ለኢትዮጵያ የጉምሩክ አስተላላፊዎች የሙያ ማህበር

<u>አዲስ አበባ</u>

ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደር እንዲሰፍን ተግተን እንሰራለን !

ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>**በያሉበት**</u>፣

ጉም-112
23/5/14

ዝፅ/ጉ/1579
29-03-14

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር ማ/ኢ30/ገ/4088
Ref.No
ቀን 23/5/2014
Date

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

በደብዳቤ ቁጥር ማኢ.30/47/57 በቀን 24/09/2013 በተፃፈ ደብዳቤ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሲፈቀድ ተሽከርካሪዎች ያገለገሉ ከሆነ ለኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ መሰረት ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው መሆኑ መገለፁ ይታወሳል። በተጨማሪም በታሪፍ መፅሐፉ ትራክተር አንቀፅ 87.01፣ የቆሻሻ ማስወገጃ ማሽነሪዎች እና ደሊቨሪ ቫን አንቀፅ 87.04 እና 87.05 የሚመደቡትን እና አምቡላንስ በሚመለከት ከዚህ በፊት በተላለፉ ደብዳቤዎች በግልፅ አለመካተታቸው ጥያቄዎች እየተነሱ ስለመሆናቸው ለመረዳት ተችለዋል።

ስለሆነም በታሪፍ መፅሐፉ ትራክተር በአንቀፅ 87.01፣ የቆሻሻ ማስወገጃ ማሽነሪዎች እና ደሊቨሪ ቫን በአንቀፅ 87.04 እና 87.05 የሚመደቡ እና አምቡላንስ ይህ ደብዳቤ እስከወጣበት ቀን ድረስ የተጫኑ ሆነው ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ለመጨረሻ ጊዜ ፀንተው ስራ ላይ ባሉ ህጎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ ሲፈቀድ የአገልግሎት ዘመን መሰረት ተደርጎ ከተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ጭምር ነፃ እንዲሆኑ የተፈቀደ መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No 1